# የ COVID-19 የቅድመ-ተጋላጭነት ፕሮፊላክሲስ ምን ማለት ነው?

## ቫይረስ ከሰው ህዋሳት ጋር ከመጣበቅ እና ከመግባት ለመከላከል የተዘጋጀ መድሃኒት ነው። ይህ ሰውነትን ከበሽታ ይከላከላል።



**12 አመት እና ከዚያ በላይ የሆናቸው ሰዎች እንደሚከተሉት ከሆኑ COVID-19 ን ለመከላከል ለቅድመ-ተጋላጭነት ፕሮፊላክሲስ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ፦**

- ቢያንስ ክብደታቸው 88 ፓውንድ (40 ኪግ) ከሆነ።
- በአሁኑ ሰዓት በ COVID-19 ካልታመሙ።
- ከመካከለኛ እስከ ከባድ ደካማ በሽታ የመከላከል አቅም ካላቸው።
- በጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ የ COVID-19 ክትባትን ለመቀበል ምክር ካልተሰጥዎት።

### በቅርቡ የ COVID-19 ክትባትን ከተቀበልኩ የ COVID-19 የቅድመ-ተጋላጭነት ፕሮፊላክሲስን መውሰድ እችላለሁ?

የቅድመ-ተጋላጭነት ፕሮፊላክሲሱ የሰውነትዎን የ COVID-19 በሽታ የመከላከል አቅም ግብረ መልስ ሊቀንስ ይችላል። ይህን ህክምና ለመውሰድ ከ COVID-19 ክትባትዎ በኋላ ቢያንስ ለሁለት ሳምንታት መጠበቅ አለብዎት።

### የምወስደው እንዴት ነው?

2 የተለያዩ በጡንቻ ውስጥ (በጡንቻዎች ውስጥ ዘልቆ የሚሰጥ መድሃኒት) የሚሰጡ መርፌዎችን ይወስዳሉ።

### ወጪው ምን ያክል ነው?

መድሃኒቱ በራሱ ከፌደራል መንግስት በነጻ ይቀርባል። እያንዳንዱ አቅራቢ በታካሚው በጋራ የመከፈል ዕድል ያለው በመድህን አቅራቢዎ የሚከፈል የመርፌ ክፍያን ሊያስከፍል ይችላል።

Washington State Department of Health

DOH 825-030 March 2022 Amharic

ይህን ሰነድ በሌላ ቅርጸት ለመጠየቅ፣ 1-800-525-0127 ላይ ይደውሉ። መስማት ለተሳናቸው ወይም መስማት ለሚቸገሩ ደንበኞች፣ እባክዎ በስልክ ቁጥር 711 (Washington Relay) ይደውሉ ወይም በ civil.rights@doh.wa.gov ኢሜይል ይላኩ።